# ከጉዲፈቻ በኋላ – ጥያቄዎች እና መልሶች

ስለ ጉዲፈቻ የድጋፍ ፕሮግራም ላሉ ጥያቄዎች የሚሆኑ መልሶች፣ እና ልጅዎን ለማሳደግ የሚረዱዎት ሃብቶች ሊገኙ የሚችሉ ሃብቶች።



Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

# መግቢያ

በጉዲፈቻ ለማሳደግ ላደረጉት ዉሳኔ እንኳን ደስ አልዎት። በጉዲፈቻ ልጁን በማሳደግዎ፣ ከልጅዎ ጋር ስሜታዊ፣ማህበራዊ እና ህጋዊ ግንኙነቶችን መስርተዋል።

ልጅን ማሳደግ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በ1971 የWashington State(ዋሽንግተን ስቴት) ህግ አውጭ አካል ልዩ ፍላጎት ላላቸው ልጆች ጉዲፈቻ እንዲደረግ የAdoption Support Program(ማደጎ ድጋፍ ፕሮግራም) ለማቋቋም የጉዲፈቻ ድጋፍ ማሳያ ህግን አፀደቀ። በኋላ በ1980 የፌደራል መንግስት የ1980-PL 96-272 የጉዲፈቻ እርዳታ እና የህጻናት ደህንነት ህግን አፀደቀ፣ ይህም ለጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም የፌደራል የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል።

Department of Children, Youth, and Families(የህጻናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች መምሪያ, DCYF) ጉዲፈቻውን ከማጠናቀቅዎ በፊት ከእርስዎ ጋር ውል በመግባት የማደጎ ድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ይህ የስምምነት ውል DCYF ከጉዲፈቻ በኋላ ለህክምና ሽፋን፣ ለምክር፣ ለተመረጡት በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ የሕክምና ዕርዳታዎችን እናም ስምምነት ላይ ከተደረሰ የልጅዎን



ፍላጎቶች ለማሟላት እርስዎን ለመርዳት ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ እንዲያቀርብ ያስችለዋል።

ይህ ቡክሌት ስለ ጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ እና ልጅዎን በማሳደግ ረገድ ሊረዱዎት የሚችሉ የማህበረሰብ ምንጮችን(ሪሶርሶችን) ለይተው እንዲያውቁ ይረዳዎታል። እንዲሁም የማደጎ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪዎ ከፖርግራሙ ሃብቶች ጋር በተያያዘ ጥያቄዎቹን ለመመለስ የሚገኝ ይሆናል።

# ይዘቶች


ጥያቄዎች እና መልሶች ........ 2

የጉዲፈቻ ድጋፍ ሰራተኞችን ማግኘት ........ 2

የጉዲፈቻ ድጋፍ ስምምነት ........ 3

የፕሮግራሙ ጥቅማጥቅሞች ........ 4

- ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ ........ 4
- ሜዲካል ........ 6
- ስለ Medicaid ያሉ ተጨማሪ መረጃዎች፡- ........ 7
- የጥርስ እንክብካቤ ........ 7
- ABCD – የሕጻናት እና ወጣት ልጆች የጥርስ ሕክምና ........ 7
- ሕክምናዎችን ማግኘት ........ 7
- የአይን ፈተና እና የአይን መነጽርዎች ........ 7
- የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶች ........ 8
- ትምህርት ........ 11
- ያማመልከቻ ሂደት ........ 11
- ይየብቁነት ወጪዎች ........ 12
- በፖርግራሙ ውስጥ የሚፈለጉ መስፈርቶች እና ቀጣይነት ያላቸው ተሳትፎዎች ........ 12
- የጉዲፈቻ ማጠናቀቅያ ወጪዎች ........ 12
- ስልጠና ........ 12

ተጨማሪ መረጃዎች ........ 13

ከክልሉ ወጣ ሲሉ ........ 14

የማህበረሰብ አገልግሎቶች/ድጋፍዎች ........ 14

የኦንላይን(የመስመር ላይ) ሪሶርሶች ........ 15


# ጥያቄዎች እና መልሶች

## የጉዲፈቻ ድጋፍ ሰራተኞችን ማግኘት



**Q:** ስለ ስምምነቴ ወይም አገልግሎቶቼ ጥያቄ ሲኖረኝ ማንን ማነጋገር አለብኝ?

**A:** ስምምነትዎን ያደራደውን ሰው ያግኙ። ውልዎን የተደራደረውን ሰው ካላወቁ፣ 1-800-562-5682 ይደውሉ፣ የተቀዳውን መልእክት በጥሞና ያዳምጡ እና መጠየቂያዎቹን ይከተሉ። ከWashington(ዋሽንግተን) ግዛት ውጭ የሚኖሩ ከሆነ በመጀመሪያ ስምምነትዎ የረዳዎትን አማካሪ ያነጋግሩ።



## የጉዲፈቻ ድጋፍ ስምምነት

**Q:** የጉዲፈቻ ድጋፍ ስምምነት ምንድን ነው?

**A:** የጉዲፈቻ ድጋፍ ስምምነት በእርስዎ እና በDCYF መካከል የሚደረግ ሕጋዊ ኮንትራክት ነው። ስምምነቱ እርስዎ እና መምሪያው በጉዲፈቻ የድጋፍ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ መከተል ያለብዎትን ውሎች እና ሁኔታዎች ይሰያል።

**Q:** ስምምነቱ መቼ ነው ተግባራዊ የሞሆነው?

**A:** በስምምነቱ ውስጥ ተቃራኒው ካልተገለጸ በቀር ውሉ ተግባራዊ የሚሆነው ጉዲፈቻው ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ነው።

**Q:** ያሳደኩት ልጅ እድሜው ከ 13 ዓመት በላይ ከሆነስ፣ ያ ድጋፉ ላይ ለውጥ ይኖረዋል?

**A:** ልጅን ከ13 ዓመት እስከ 17 ዓመት የማደጎ ልጅ ከወሰዱ፣ ልጁ ለFree Application for Federal Student Aid(ለፌዴራል የተማሪ እርዳታ ነጻ ማመልከቻ፣ FASFA) ራሱን የቻለ ሰው ተደርጎ ይወሰዳል። ከ14 እስከ 17 አመት እድሜ ያለው ልጅ በጉዲፈቻ እያሳደጉ ከሆነ፣ ለCollege Bound ስኮላርሺፕ ፕሮግራም ለማመልከት ልጁ ብቁነቱ እንደተጠበቀ ነው የሚሆነው። ከ 16 ዓመት እስከ 17 ዓመት የሆነ ልጅን በጉዲፈቻ ከወሰዱ፣ ልጁ የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ከሆነ እስከ 21 አመት ድረስ ባለው የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም ውስጥ መቀጠል ይችል ይሆናል።

- የሃይስኩል ወይም የሃይስኩል ትምህርት ቤት ተመጣጣኝ የምስክር ወረቀት ፕሮግራም/GED ውስጥ ያለ ተሳትፎ።
- የኮሌጅ ወይም የሙያ ትምህርት ቤት ፕሮግራም መከታተል፣ ወይም አመልክቶ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በጊዜ የመመዝገብ ፍላጎት ማሳየት ይችላል።
- ለስራ መሰናክሎችን ለማስወገድ በሚያግዝ የስራ ስልጠና ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ።
- በወር ከአሥራ ስምንት ሰዓት እና ከዝያ በላይ ቅጥር ውስጥ መሳተፍ።
- በተመዘገበው የሕክምና ሁኔታ ምክንያት፣ አንድ ወጣት ከላይ በተጠቀሱት የብቃት ምድቦች ውስጥ መሳተፍ አይችልም።

በተጨማሪም፣ በተራዘመው የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም ውስጥ ያሉ ወጣቶች ለEducation and Training Voucher Program(የትምህርት እና ስልጠና ቮውቸር ፕሮግራም፣ ETV) ብቁ ሲሆኑ ይችላሉ። በዚህ ርዕስ ላይ ያለው ተጨማሪ መረጃ በ Education (ትምህርት) የሚለው ክፍል ውስጥ ይገኛል።

**Q:** ስምምነቱ መቼ ነው የሚያበቃው?

**A:** ስምምነቱ የሚያበቃ፣ የሚከተሉት ነገሮች ሲሆኑ ነው፦

- የማደጎ ልጅ 18 ዓመት ሲሞላው (ልጁ የሙሉ ጊዜ የትምህርት መርሃ ግብር ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተመጣጣኝ የምስክር ወረቀት/GED እየሰራ ካልሆነ በስተቀር)።
- ወላጆች ወይም ልጅ ሲሞቱ።
- እርስዎ ከአሁን በኋላ በሕግም በገንዘብም ለልጁ ተጠያቂ በማይሆኑበት ጊዜ።
- በጉዲፈቻ ከ16 እስከ 17 ዓመት የሆነ ልጅ ከ18 ዓመት በኋላ በተዘረጋው የጉዲፈቻ ድጋፍ ስምምነት ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች በማያሟለበት ጊዜ።

**Q:** ልጄ 18 ዓመት ሳይሞላው የፕሮግራሙ መቋረጥን በተመለከተ ማስታወቂያ ይደርሰኛል?

**A:** ስምምነቱ በልጁ 18ኛ የልደት ቀን እንደሚያልቅ የሚጠቁም ማሳወቂያ ሊደርስዎት ይችላል። የልጅዎን 18ኛ የልደት ቀን ቢያንስ 90 ቀናት ቀደም ብሎ የማደጎ ድጋፍ ፕሮግራሙን ማግኘት የእርስዎ ኃላፊነት ነው። ፕሮግራሙ ከእርስዎ ካልሰማ በስተቀር፣ የማደጎ ድጋፍ ጥቅማጥቅሞች በልጅዎ 18ኛ የልደት ቀን ወድያዉኑ ይቆማሉ።

**Q:** ልጄ 18 አመት ከሆነ እና አሁንም የሙሉ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ከሆነ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመጣጣኝ የምስክር ወረቀት ለማጠናቀቅ የሙሉ ጊዜ እየሰራ ከሆነስ?

**A:** ጉዳዩ ይህ ከሆነ፣ ልጁ 18 ዓመት ሳይሞላው፣ ወላጁ የማደጎ ድጋፍ እንዲቀጥል ከጠየቁ እና ልጁ የሙሉ ጊዜ ተማሪ መሆኑን እና የሚመረቅበትን ቀን የሚገልጽ ደብዳቤ በትምህርት ቤቱ ደብዳቤ ላይ ከደረሰ፣ ልጅዎ በፕሮግራሙ ውስጥ ሊቆይ ይችላል።



**Q:** የስምምነቱን ማሻሻያ መጠየቅ እችላለሁ?

**A:** በቤተሰብ ሁኔታ ወይም በልጁ ሁኔታ ላይ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ፣ ለጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪዎ በመጻፍ ስምምነቱን እንዲከልስ መጠየቅ ይችላሉ። የእርስዎ አማካሪ የልጅዎን ልዩ ፍላጎቶች እና የቤተሰብዎን ወቅታዊ ሁኔታዎች በተመለከተ ማስገባት ስለሚፈልጉ ሰነዶች ምክር ይሰጥዎታል።

**Q:** የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪውን ወዲያውኑ ለማሳወቅ በሁኔታዎች ላይ ምን ለውጦች ያስፈልጋሉ?

**A:** የሚከተለው ሲከሰት የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪውን ወዲያውኑ ያሳውቁ:-

- ልጁ ከአሁን በኋላ በቤትዎ ውስጥ አይኖርም።
- እርስዎ ከአሁን በኋላ በሕግ ለልጁ ተጠያቂ በማይሆኑበት ጊዜ።
- በቋሚ አድራሻዎ ላይ ለውጥ ሲኖር።
- ልጁ ወይም ወላጁ ሲሞት።
- በወላጆች የጋብቻ ሁኔታ ላይ ለውጥ ሲኖር።
- በልጁ ህጋዊ ወይም አካላዊ ጥበቃ ላይ ለውጥ ሲኖር።
- ልጁ ለሌላ የፌደራል መርሃ ግብር፣ ማለትም የSocial Security benefits(ሶሻል ሴኪዩሪቲ ጥቅማጥቅሞች) ፣ Supplemental Security Income(የተጨማሪ ሴኪዩሪቲ ገቢ፣ SSI) ጥቅማጥቅሞች፣ Veteran's Administration benefits(የአርበኞች አስተዳደር ጥቅማጥቅሞች)፣ ወይም Temporary Aid to Need Families(ለቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ፣ TANF) ብቁ በሚሆንበት ጊዜ።

## የፕሮግራሙ ጥቅማጥቅሞች

### ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ

**Q:** የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራሙ ልጄን ለማሳደግ ሁሉንም ወጪዎች ይሸፍንልኛል?

**A:** እንደ ወላጅ(ዎች)፣ እርስዎ ለልጅዎ ፍላጎቶች በገንዘብ ተጠያቂ ነዎት የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም የልጅዎን ተራ እና ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት እርስዎን ለመርዳት ሃብቶቻችሁን በማጣመር መሆን አለበት። የልጅዎን ፍላጎቶች ለማሟላት እርስዎ የሚፈልጉት የድጋፍ መጠን የሚወሰነው በእርስዎ እና በጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪ መካከል በሚደረግ ውይይት እና ድርድር ነው።

**Q:** ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያን በሚደራደሩበት ጊዜ፣ ምን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብኝ?

**A:** የልጅዎን የድጋፍ ስምምነት መደራደር ሲጀምሩ፣ ሊታሰቡ የሚችሉ ሦስት ነገሮች አሉ:-

- የልጁን ልዩ ፍላጎቶች ሊያሟሉ የሚችሉ ወጪዎች።
- የቤተሰቡ ሁኔታ(ገደብ)።
- በRCW የተፈቀዱ ከፍተኛ የህግ አውጭዎች።

ስለ ልዩ የሕክምና፣ የአካል ወይም የስሜታዊ ፍላጎቶች የልጅዎ ፍላጎቶች። "የቤተሰብ ሁኔታዎች" የልጁን ፍላጎቶች በቤተሰብ ሁኔታ ውስጥ ለማካተት፣ በፌዴራል Children's Bureau(የሕጻናት ቢሮ) የቤተሰብ አቅም ማለት እንደሆነ ተገልጸዋል። ገቢ፣ ዕዳ፣ መኖሪያ ቤት፣ መጓጓዣ፣ ቦታ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ የወላጅነት ሙያ፣ የወላጅ ጤና ፍላጎቶች፣ የሌሎች የቤተሰብ አባላት ፍላጎቶች እና ማንኛውም ሌሎች ምክንያቶች ይታሰባሉ። ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያዎችን ለመወሰን ምንም የተቀናጀ ቀመር የለም።

የልጅዎ ፍላጎት ወይም የቤተሰብ ሁኔታ ከተቀየረ ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ ስምምነቱን በማሻሻል ሊለወጥ እንደሚችል ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ወርሃዊ የጥሬ ገንዘብ ክፍያ በሚገመቱ ችግሮች ላይ የተመሰረቱ አይደሉም።

*ልጁ በማደጎ ውስጥ ከሆነ፣ የWashington ስቴት ህግ አውጭ አካል ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ መጠን አንድ ልጅ ሊያገኘው ከሚችለው ከፍተኛው የማደጎ እንክብካቤ ወጪ ገድቧል። ከዚህ የተነሳ፣ በድርድር የተደረገው መጠን ከ$0 ሊጀምር ይችላል እና ከህግ አውጭው ከፍተኛው መብለጥ አይችልም። የሕግ አውጭው ከፍተኛው በጉዲፈቻ ጊዜ በልጁ ዕድሜ ላይ የተመሰረተ ነው።*



**Q:** የጉዲፈቻ ድጋፍ ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ እንዴት ነው የሚወሰነው?

**A:** ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ በአሳዳጊ ወላጆች እና በDCYF Adoption Support Consultant(የማደጎ ድጋፍ አማካሪ) መካከል በሚደረግ ድርድር ነው የሚወሰነው። ክፍያው ረዘም ላለ ጊዜ የታቀደውን የሕፃኑን መደበኛ እና ልዩ ፍላጎቶች ለመሸፈን ከወላጆች ሀብቶች ጋር ይጣመራል እና የሚጠበቁ ፍላጎቶችን መሸፈን የለበትም።

ስምምነቱ የተለያዩ የቤተሰብ-ተኮር ሁኔታዎችን ይመለከታል፡-

- የቤተሰቡ ብዛት።
- የተለመደ የመኖርያ ወጪ።
- የማንኛውም ቤተሰብ ልዩ ፍላጎቶች።
- የቤተሰብ ገቢ።
- የቤተሰብ ግበዓቶች(ሪሶርሶች) እና የቁጠባ እቅዶች።
- የሜዲካል እና የሆስፒታል ውስጥ ሕክምና ፍላጎቶች።
- የቤተሰብ እንክብካቤ የመግዛት ወይም የመቀበል ችሎታ።
- ለማደጎ ልጅ የሚያስፈልጉ ሌሎች ወጪዎች።

በጉዲፈቻ ድጋፉ ውስጥ በቤተሰብ መካከል ወጥነት ያለው ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ የፕሮግራሙ ግብ እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ተመሳሳይ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች እና ተመሳሳይ ሁኔታዎች በተመሳሳይ የእርዳታ ዓይነቶች ወይም መጠን ላይ መስማማት አይችሉም። የእያንዳንዱ ልጅ/ቤተሰብ ሁኔታ ልዩነት ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያን ይወስናል።

*የተገኘው መረጃ፡- 42 U.S.C. § 673 (a), 42 U.S.C. § 673 (a) (3), የልጆች ደህንነት ፖሊሲ መመሪያ 8.2D.4 (Q.1), WAC 110-80-0220 እና RCW 74.13a.025.*

**Q:** ለእያንዳንዱ የማደጎ ልጅ በጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም በኩል ከወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ በተጨማሪ ምን ጥቅማጥቅሞች ይሰጣሉ?

- በMedicaid በኩል የህክምና እና የጥርስ ጥቅሞች።
- አስቀድሞ የተፈቀደ የምክር እርዳታ።
- በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ የሕክምና ጣልቃገብነቶች።
- ለጉዲፈቻ ወጪዎች፣ ለአንድ ልጅ እስከ 1500 ዶላር የሚደርስ ክፍያ።

## ህክምና

**Q:** Washington Apple Health (Medicaid) በጉዲፈቻ ድጋፍ ላይ ለልጆች የሚሰጠው ምን ዓይነት ሽፋን ነው?

**A:** Apple Health (Medicaid) ያለ ምንም ወጪ የሚቀርብ ሲሆን ልጅዎን በሚከተሉት ይሸፍናል:-

- በCoordinated Care of Washington(ዋሽንግተን የተቀናጀ እንክብካቤ፣ CCW)፣ Apple Health Core Connections(የአፕል ሄልዝ ዋና ግንኙነቶች፣ AHCC) በተባለው ፕሮግራም አማካኝነት እንደ ዋና ኢንሹራንስ ለሁለቱም የአካል እና የባህርይ ጤና ወይም
- ልጅዎን በግል የጤና እቅድዎ ውስጥ ካስቀመጡት በሚከተሉት ሁለተኛ ደረጃ የኢንሹራንስ ፕሮግራሞች:-
  - ProviderOne(የአገልግሎት ክፍያ) ለአካላዊ ጤና።
  - ለባህሪ ጤና፣ በMedicaid Managed Care Organization(በMedicaid የሚተዳደር እንክብካቤ ድርጂት፣ MCO) ለ Behavioral Health Services Only(ለባህሪ ጤና አገልግሎት ብቻ፣ BHSO)። በአብዛኛዎቹ ክልሎች የተመደበው MCO Cordinated Care(የተቀናጀ እንክብካቤ) ይሆናል።



**Q:** በApple Health (Medicaid) የሚሸፈኑት አገልግሎቶች ምን ምን ናቸው?

**A:** ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የአካል እና የባህሪ ጤና አገልግሎቶች በ Apple Health ለጉዲፈቻ ድጋፍ ቤተሰቦች ይሸፈናሉ:-

- Applied Behavioral Analysis(የተተገበረ የባህሪ ትንተና)
- Behavioral Health(የባህሪ ጤና)
  - በሆስፒታል ውስጥ ተኝተው የሚታከሙ ታካሚዎች
  - ከሆስፒታል ዉጪ የሚታከሙ ታካሚዎች
  - Wraparound with Intensive Services (የጠንካራ አገልግሎቶች መጠቅለያ፣ WISe)
  - Substance Use Disorder (የንጥረ ነገር አጠቃቀም ዲስኦርደር፣ SUD) ሕክምና
  - የሳይካትሪ(ስነ አዕምሮ አገልግሎቶች)
  - የቤተሰብ ቴራፒ
  - የወላጅነት ጣልቃ ገብነት (Triple P፣ Incredible Years፣ PCIT፣ ወዘተ)
- የጥርስ ሕክምና
- ዶክቶሮች/አቅራቢዎች
- የአደጋ ጊዜ ክፍል
- EPSDT (ዕድሜያቸው እስከ 21 ዓመት ለሆኑ ሕፃናት የጤንነት ምርመራ እና የመከላከያ እንክብካቤ)
- የአይን መነጽሮች እና የአይን ፈተና
- Gender Affirming Medical Care(ሥርዓተ-ፆታን የሚያረጋግጥ የሕክምና እንክብካቤ)
- የቤት ውስጥ ጤና አገልግሎቶች
- የአስተርጓሚ አገልግሎቶች ለህክምና አገልግሎት
- የሕክምና መሳሪያዎች እና አቅርቦቶች
- የመድሃኒት ማዘዣዎች
- ቀዶ ጥገና
- ትራንስፖርቴሽን(በክልል ደላሎች በኩል)

አንዳንድ አገልግሎቶች ገደቦች አሏቸው። ለበለጠ መረጃ ከህክምና አቅራቢዎ ጋር ያረጋግጡ ወይም የHealth Care Authority የደንበኞች አገልግሎት ማእከልን በ1-800-562-3022፣ ኤክስቴንሽን 15480ን ወይም ልጅዎ የCCW-AHCC አባል ከሆነ 1-844-354-9876 ወይም **AHCCTeam@coordinatedcarehealth.com** ያግኙ።

**Q:** በWashington Apple Health/Medicaid በኩል የህክምና አገልግሎት እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

**A:** ጉዲፈቻው እንደተጠናቀቀ እና የልጅዎን ስም በSocial Security Administration(ሶሻል ሴኩሪቲ አስተዳደር) ካዘመኑት፣ የልጅዎን የዘመነ የProviderOne ሽፋን እና ካርድ ለመጠየቅ የFoster Care Medical Team(ፎስተር ኬር ሜዲካል ቡድንን፣ FCMT) በስልክ ቁጥር 1-800-562-3022 ኤክስቴንሽን 15480 ማነጋገር ይችላሉ።

በWashington ውስጥ የጉዲፈቻ ድጋፍ ቤተሰቦች ሽፋናቸውን በሚተዳደረው የእንክብካቤ እቅድ በኩል በCoordinated Care of Washington(የተቀናጀ ዋሽንግተን እንክብካቤ)፣ Apple Health Core Connections (የአፕል ጤና ዋና ግንኙነቶች) (CCW-AHCC) ሊያገኙ ይችላሉ። ልጅዎ የCCW-AHCC አባል ከሆነ፣ እነሱ በፖስታ እና በስልክ ያገኙዎታል፣ ወይም እርስዎ CCW-AHCCን በቀጥታ በስልክ 1-844-354-9876 እና **AHCCTeam@coordinatedcarehealth.com** በኩል ማግኘት ይችላሉ።

**Q:** ለምንድነው የ ProviderOne አገልግሎቶች ካርድ የሚያስፈልገኝ?

**A:** ይህ የልጅዎ የህክምና መታወቂያ ካርድ ነው፣ ይህም ልጅዎ በMedicaid በኩል በህክምና እርዳታ ላይ መሆኑን ያረጋግጣል። ልጅዎ በግላዊ መድንዎ የተሸፈነ ከሆነ፣ ይህ ካርድ በMedicaid ለተሸፈኑ አገልግሎቶች የጋራ ክፍያ/ተቀናሽ (ከኪስ ወጭ የላችሁም) እንደማይከፍሉ ያረጋግጣል። ልጅዎ በ CCW-AHCC በኩል ኢንሹራንስ ከተገባ፣የፕሮቪደንት ኦን አገልግሎት ካርድ ለጥርስ ህክምና፣ለዓይን መነፅር እና ለመጓጓዣ አገልግሎት ይውላል።

**Q:** ካርዱ የሚያበቃበት(ኤክስፓይድ የሚያረግበት) ቀን አለው?

**A:** የ ProviderOne ካርድ የሚያበቃበት(ኤክስፓይድ የሚያረግበት) ቀን የለውም። የሽፋን ዋስትና አይደለም ነገር ግን የልጅዎን የ ProviderOne ቁጥር ለመከታተል ይጠቅማል።

**Q:** በProviderOne አገልግሎቶች ካርድ ላይ ስህተቶች ቢኖሩስ?

**A:** በካርዱ ላይ ያለው ነገር ሁሉ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ የልጅዎን ካርድ በጥንቃቄ ያረጋግጡ። በካርዱ ላይ ያለው ነገር የተሳሳተ ከሆነ ወይም መለወጥ የሚያስፈልገው ነገር ካለ ለጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪዎን ደውለው ያነጋግሩ።

**Q:** የልጄ የProviderOne አገልግሎት ካርድ ቢጠፋብኝስ?

**A:** ካርድዎ ከጠፋብዎት፣ ለ FCTM በ 1-800-562-3022፣ ኤክስቴንሽን 15480፣ ወይም የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪ ይደውሉ።

**Q:** ልጄ የግል ኢንሹራንስ እና Washington Apple Health/Medicaid ማግኘት ይችላል?

**A:** ልጅዎን በግል ኢንሹራንስዎ ውስጥ እንዲመዘገቡ ይበረታታሉ። የግል ኢንሹራንስዎ የመጀመሪያ ደረጃ ሲሆን የWashington Apple Health/Medicaid ሁለተኛ ደረጃ ነው። ሌላ የጤና ኢንሹራንስ ካለዎት፣ እባክዎን ለFCMT ያሳውቁ። ወደ1-800-562- 3022፣ ኤክስቴንሽን 15134 ይደውሉ። HCA የመጀመርያ እንሹራንስዎን ያረጋግጣል።

## ስለ Medicaid ያሉ ተጨማሪ መረጃዎች:-

### የጥርስ እንክብካቤ

የጥርስ ሕክምና ዴንቲስትን መፈለግ ከባድ ሊሆን ይችላል። የጥርስ ሀኪም ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ ወይም ወደ ጥርስ ሀኪም ማጓጓዝ ከፈለጉ በአካባቢዎ ያሉ የWashington Apple Health የሚወስዱ የጥርስ ሀኪሞች ዝርዝር ለማግኘት ወደ የህክምና እርዳታ የእርዳታ መስመር ይደውሉ። በ CCW-AHCC በኩል አገልግሎቶችን እየተቀበሉ ከሆነ ፕሮግራሙ የጥርስ ሀኪምን ለማግኘት ይረዳዎታል፣ ወደ 1-844-354-9876 ይደውሉ።

### ABCD – የሕጻናት እና ወጣት ልጆች የጥርስ ሕክምና

Access to Baby and Child Dentistry (የሕፃን እና የሕፃናት የጥርስ ሕክምና ተደራሽነት፣ ABCD) እስከ ስድስት አመት ለሆኑ ህጻናት የጥርስ ህክምና ፕሮግራም ነው። መረጃ በ **http://abcd-dental.org** ላይ ይገኛል።

### ሕክምናዎችን ማግኘት

በWashington Apple Health ለተሸፈኑ የሐኪም ማዘዣዎች የጋራ ክፍያ አይኖርዎትም። በWashington Apple Health ያልተሸፈኑ መድኃኒቶች ወጪ ሊጠይቁ ይችላሉ። መድሃኒት የተከፈለልዎት መሆኑን የፋርማሲስትዎ ሊነግርዎት ይችላል።

### የአይን ፈተና እና የአይን መነጽርዎች

አመታዊ የአይን ምርመራዎች እንደ የዓይን መነፅር እና መተኪያ መነጽሮች በሽፋኑ ውስጥ ተካትተዋል። የጤና ችግር ካለበት፣ ልጅዎ ከ6 እስከ 20 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙ ጊዜ ፈተናዎችን መውሰድ ይችል ይሆናል።

## ያአዕምሮ ጤና አገልግሎቶች

ለልጅዎ የአእምሮ ጤና ፍላጎቶች አገልግሎቶች በሁለቱም በ ProviderOne እና በCoordinated Care of Washington – Apple Health Core Connections (የተቀናጀ የዋሽንግተን እንክብካቤ - የአፕል ሄልዝ ዋና ግንኙነቶች፣ CCW-AHCC) በኩል የሚሸፈኑ ይሆናሉ። ይህንን ፍላጎት ለማገዝ እባክዎን የመጀመርያውን ሸፋን ሰጪዎን ያነጋግሩ። ልጅዎ በ CCW-AHCC የተመዘገበ ከሆነ፣ የባህሪ ጤና ክሊኒኮችን ጨምሮ ራሱን የቻለ የጤና እንክብካቤ አስተባባሪዎች ቡድን አሏቸው። የ AHCC ሰራተኞች ተገቢ አገልግሎቶችን እና አቅራቢዎችን ለመለየት፣ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ልምዶችን በማገናኘት፣ ስልጠና እና ድጋፍ ለመስጠት፣ የእንክብካቤ ስርዓት ለመዘርጋት፣ ራስን የማጥፋትን፣ የመንፈስ ጭንቀትን፣ ጭንቀትን እና እፅን የመጠቀም አደጋን ለማጣራት ሊረዱ እንዲሁም ከApple Health ሽፋንዎ የተሻለውን እንዲያገኙ ማገዝ ይችላሉ። ወደ 844-354-9876 ይደውሉ ወይም በኢሜል ወደ **AHCCTeam@coordinatedcarehealth.com** ይላኩ እና የጤናእንክብካቤ አስተባባሪዎን ይጠይቁ።

**Q:** አንድ ልጅ የአእምሮ ጤና አገልግሎት መፈለጉ የተለመደ ነገር ነው?

**A:** በመስከረም(ሴፕቴምበር) 2019 የተሻሻለው ከNational Alliance on Mental Illness(ብሔራዊ የአእምሮ ሕመም ጥምረት) የተገኘ አኃዛዊ መረጃ ከስድስት ወጣቶች መካከል አንዱ ከ6 እስከ 17 ዓመት የሆኑ ወጣቶች በየዓመቱ የአእምሮ ጤና መታወክ ያጋጥማቸዋል።

**Q:** ከጉዲፈቻ በኋላ ልጅዎ የአእምሮ ጤና ባለሙያ ማየት ቢፈልግስ?

**A:** ልጅን በማሳደግ ልብዎን እና ቤትዎን ሲከፍቱ፣ ልጅዎን ስታሳድጉ ልዩ ደስታዎችን እና ፈተናዎችን ታገኛላችሁ. ምንም እንኳን ጉዲፈቻው ከተፈጸመ ከዓመታት በኋላ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች አያስፈልጉም ቢሉም፣ አንዳንድ ጊዜ ልጅዎ በስሜት፣ በባህሪ ወይም በእድገት ተግዳሮቶች ምክንያት የአእምሮ ጤና ባለሙያ ማግኘት ሊኖርበት ይችላል። ምናልባት ልጃችሁ ሲያድግ በተለይ በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያሉ ችግሮች እየታዩ መሆኑን ሊያስተውሉ ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ የትኞቹ ጉዳዮች ለሁሉም ልጆች የተለመዱ እንደሆኑ እና የትኞቹ ጉዳዮች በተለይ ከጉዲፈቻ ከተወሰዱ ሕፃናት ጋር እንደሚዛመዱ ለመለየት ይረዳል። አብዛኛውን ጊዜ፣ ከጉዲፈቻ በኋላ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች በዋና መድንዎ፣ Medicaid (ProviderOne in Washington) ወይም እንደ ቅድመ ፍቃድ አገልግሎት በጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም ይሸፈናሉ።

**Q:** ለልጅዎ የአእምሮ ጤና አቅራቢ ማግኘት ያለብዎት መቼ ነው?

**A:** ልጅዎ በቤት፣ በትምህርት ቤት ወይም ከጓደኞችዎ ጋር ስላለው ባህሪ የሚያሳስብዎት ነገር ካለ የልጅዎን የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ያነጋግሩ። ወቅታዊ የሆነ የሰለጠነ አማካሪ ወይም የቴራፒስት እርዳታ የመጀመርያውን ችግር ይበልጥ አሳሳቢ ከመሆኑ በፊት ሊፈታ ይችላል። ለምሳሌ፣ ልጅዎ የሚከተለው ስላለው የአእምሮ ጤና አገልግሎት ሊፈልግ ይችላል።

- በትምህርት ቤት ውስጥ ጉልህ የሆነ የውጤት ውድቀት።
- ስለ ነገሮች ተጨንቀሃል እና ተጨንቀሃል።
- እንቅልፍ የመተኛት ችግር በተደጋጋሚ መንቃት ወይም ብዙ ጊዜ ቅዠት ነው።
- አዝኗል፣ ስሜቱ የተነካ ወይም የተናደደ ነው።
- ደካማ በራስ መተማመን።
- የዕለት ተዕለት ችግሮችን መቋቋም አልቻለም።
- አደንዛዥ ዕፅ ወይም አልኮል አላግባብ መጠቀም ጀመሯል/ች።
- እራሳቸውን መጉዳት ጀምረዋል።
- ያልተለመዱ ሀሳቦች ወይም ባህሪዎች
- የአመጋገብ ልማድ ለውጥ።
- ከጓደኞች ፣ ከቤተሰብ እና ከመደበኛ እንቅስቃሴዎች መውጣት።
- ስለ አካላዊ ምልክቶች ተደጋጋሚ ቅሬታዎች እንደ የሆድ ህመም፣ ራስ ምታት፣ ድካም፣ ወዘተ ከስሜት ጋር ይዛመዳሉ።
- እንደ “ምነው በሞትኩ” ወይም “ምነው ተኝቼ ሳልነቃ በቀረው” አይነት ያሉ አስተያየቶችን መስጠት።
- ማንኛውም በባህሪ፣ በእንቅስቃሴ ወይም በማህበራዊ ቡድኖች ላይ የሚታይ ከባድ ለውጥ (የህገወጥ ዝውውር አመላካቾች ሊሆን ይችላል)።

**Q:** የአእምሮ ጤና ባለሙያን ለልጅዎ እንዴት ማግኘት ይችላሉ?

**A:** ማንኛውንም የጤና ሁኔታ ለማስቀረት ልጅዎን አመለካከቶችን ሊያቀርብ እና ሊገመግም ከሚችለው ከልጅዎ ሐኪም ጋር ስለ ስጋቶችዎ ይወያዩ። አብዛኛዎቹ ዶክተሮች ከአእምሮ ጤና ስፔሻሊስቶች እንደ የልጆች ሳይኮሎጂስቶች ወይም ክሊኒካዊ ማህበራዊ ሰራተኞች ጋር የስራ ግንኙነት አላቸው፣ ስለዚህ ልጅዎ ለሚያስፈልገው እርዳታ በአካባቢዎ ወደሚገኝ የአእምሮ ጤና አገልግሎት ሰጪ ሊልኩዎት ይችላሉ። እንዲሁም፣ ጓደኞችን፣ ቤተሰብን ወይም ቀሳውስትን ስለሚመክሯቸው ብቁ ባለሙያዎች መጠየቅ ይችላሉ። አስፈላጊ ከሆነ፣ የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎ በኔትወርኩ ውስጥ ያሉትን የአእምሮ ጤና አቅራቢዎች ዝርዝር ሊሰጥዎ ይችላል።

**Q:** የአእምሮ ጤና ባለሙያን ለልጅዎ እንዴት መምረጥ አለብዎት?

**A:** ብዙ አይነት የሕክምና ዘዴዎች እና የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን የሚሰጡ ባለሙያዎች አሉ ነገር ግን በጉዲፈቻ ቤተሰቦች ላይ የሚያጋጥሟቸውን ልዩ ጉዳዮች የሚያውቅ፣ በባህል ጠንቅቆ የሚያውቅ እና ምላሽ የሚሰጥ፣ ከልጅዎ ጋር በደንብ የሚሰራ እና እርስዎን በህክምና ውስጥ የሚሳተፍ ባለሙያ መምረጥ አስፈላጊ ነው። በተለምዶ፣ እንዲህ ዓይነቱ ባለሙያ ከበርካታ የሙያ ምድቦች ውስጥ በአንዱ ውስጥ እንደሚከተሉት ይመደባል:-

- **Psychiatrist(የሥነ አእምሮ ሐኪም)**
  የአእምሮ እና የስሜት ህመሞችን ለመመርመር እና ለማከም ልዩ ስልጠና ያለው የህክምና ዶክተር ነው። የሥነ አእምሮ ሐኪም መድኃኒት ሊያዝዙ ይችላሉ, ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ታካሚዎችን የማማከር ስራን አይሰሩም።
- **የሕጻናት/አዋቂ Psychiatrist(የሥነ አእምሮ ሐኪም)**
  በልጆች ላይ ስሜታዊ እና ባህሪ ችግሮችን ለይቶ ለማወቅ እና ለማከም ልዩ ስልጠና ያለው የሕክምና ዶክተር ነው። የሕጻናት እና የጉርምስና የሥነ አእምሮ ሐኪሞች መድኃኒት ሊያዝዙ ይችላሉ፣ ነገር ግን የስነ-ልቦና ሕክምናን ላይሰጡ ይችላሉ።
- **የአእምሮ ወይም የአእምሮ ጤና ነርስ ባለሙያ**
  ተመዘገበ ነርስ በዲግሪ የተመረቀ እና የአእምሮ እና የስሜት ህመም ምርመራ እና ህክምና ልዩ ስልጠና ያለው ነው።

በተጨማሪም፣ የመጀመሪያ ደረጃ ተንከባካቢ ሐኪምዎ፣ የሐኪምዎ ረዳት ወይም ነርስ ባለሙያ (በክልልዎ ላይ በመመስረት) ብዙውን ጊዜ መድሃኒት ለማዘዝ ብቁ ናቸው።

የሚከተሉት የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች የስነ-ልቦና ምዘናዎችን እና ህክምናን ሊሰጡ ይችላሉ. ይሁን እንጂ በአጠቃላይ መድሃኒቶችን ማዘዝ አይቻልም (ምንም እንኳን አንዳንድ ግዛቶች ቢፈቅዱም):-

- ክሊኒካል ሳይኮሎጂስት– በስነ-ልቦና ውስጥ እውቅና ካለው/ ከተሰየመ ፕሮግራም በሳይኮሎጂ የዶክትሬት ዲግሪ ያለው የስነ-ልቦና ባለሙያ ነው። የሥነ ልቦና ባለሙያዎች ምርመራዎችን እንዲያደርጉ እና የግለሰብ እና የቡድን ህክምናዎችን እንዲሰጡ የሰለጠኑ ናቸው።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች ምክር ሊሰጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን መድሃኒት ማዘዝ አይችሉም:-

- Clinical Social Worker(ክሊኒካዊ የማህበራዊ ሰራተኛ) – እውቅና ካለው የድህረ ምረቃ ፕሮግራም በማህበራዊ ስራ የማስተርስ ዲግሪ ያለው አማካሪ ነው። ምርመራዎችን ለማድረግ የሰለጠኑ፣ የግለሰቦችን እና የቡድን ምክሮችን ለመስጠት እና የጉዳይ አስተዳደር እና የጥብቅና አገልግሎት ይሰጣሉ፣ እና አብዛኛውን ጊዜ በሆስፒታል ውስጥ ይገኛሉ።
- ፈቃድ ያለው የባለሙያ አማካሪ – በስነ-ልቦና፣ በአማካሪነት ወይም በተዛመደ መስክ የማስተርስ ዲግሪ ያለው አማካሪ ነው። ለመመርመር እና የግለሰብ እና የቡድን ምክር ለመስጠት ሰልጥነዋል።
- የአዕምሮ ጤና አማካሪ – የማስተርስ ዲግሪ ያለው አማካሪ እና የበርካታ አመታት በክሊኒካዊ የስራ ልምድ በማስተዳደር ያገለገለ። ለመመርመር እና የግለሰብ እና የቡድን ምክር ለመስጠት ሰልጥነዋል።

**Q:** ከአዕምሮ ጤና ባለሙያ ጋር ሲነጋገሩ ምን ማየት አለብዎት?

**A:** ከቴራፒስት ከሚፈልጉት ነገሮች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ከታካሚዎች ጋር አብሮ ለመስራት እንዴት እንደሚቀርቡ ፣ የራሳቸውን ፍልስፍና እንዲሁም ሪፖርቶችን ለእርስዎ ከሰጡ ፣ እና የማይገኙ ከሆነ ለእነሱ የሚሸፍናቸው ማወቅ ይፈልጉ ይሆናል። እንደ ቤተሰብ ወይም ልጅ ማማከር፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ማሰልጠን፣ ሀዘን እና መጥፋት፣ መተሳሰር ወይም ከአሳዳጊ ቤተሰቦች ጋር የመሥራት ልምድ ያላቸው ልዩ ሙያ እንዳላቸው መጠየቅ ይችላሉ። ለህክምና ባለሙያው ስለ ስጋቶችዎ አጭር መግለጫ መስጠት እና ልጅዎ በደል፣ ተቋማዊ አሰራር፣ ተያያዥ ጉዳዮች፣ የእድገት መዘግየቶች እና ሌሎችም ካጋጠመው እንደ ክፍት ጉዲፈቻ ያሉ የቤተሰብዎን ሁኔታ ማስረዳት ይፈልጉ ይሆናል።

ልምድ እና ትምህርት አስፈላጊ ሲሆኑ፣ ልጅዎን ለማነጋገር ምቾት የሚሰማውን
አማካሪ ማግኘትም አስፈላጊ ነው። ትክክለኛ ብቃት እና ልምድ ያለው፣ ልጅዎን አሁን ባለው ሁኔታ ለመርዳት የተሻለውን አካሄድ ይፈልጉ እና የእርስዎን ተሳትፎ እና ድጋፍ ከፍ አድርገው ይመለከቱታል።

**Q:** ልጅዎ የአእምሮ ጤና አቅራቢ ሲመርጡ ክፍያዎች እንዴት ነው የሚከፈሉት?

**A:** የመረጡት የአእምሮ ጤና ባለሙያ የእርስዎን ዋና መድን ወይም የMedicaid ሽፋን የሚቀበል መሆኑን ይወቁ እና ስለክፍያዎቻቸው ይጠይቁ። የግል ኢንሹራንስ ከሌልዎት፣ ሽፋንዎ የተገደበ ነው ወይም ቴራፒስት ኢንሹራንስዎን ወይም Medicaidዎን የማይቀበል ከሆነ፣ የእርስዎ የጉዲፈቻ ድጋፍ ስምምነት ለተመላላሽ ታካሚ የአእምሮ ህክምና እና ሌሎች የምክር አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ያረጋግጡ። እንደዛ ከሆነ፣ አገልግሎቱን ከመጀመርዎ በፊት የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪዎን ያግኙ እና ለአገልግሎቶች ቅድመ ፍቃድ ይጠይቁ።

በCCW-AHCC ውስጥ ለተመዘገቡ፣ የቅድመ ፍቃድ አገልግሎቶችን ከመጠቀምዎ በፊት፣ እባክዎን ወደ 844-354-9876 ይደውሉ ወይም የMedicaid አገልግሎት አቅራቢን ለማግኘት እርዳታ ለማግኘት AHCC በ **AHCCTeam@coordinatedcarehealth.com** ኢሜል ይላኩ።

**Q:** የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም ለአገልግሎቶች ቅድመ ፍቃድ ሂደት ምንድን ነው?

**A:** የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪውን ደውለው የቅድሚያ ፍቃድ ሲጠይቁ የስቴት ዋጋዎችን እና የተሸፈኑ አገልግሎቶችን ያሳውቁዎታል እና የቅድመ ፍቃድ ቅጹን ይላክልዎታል። የቅጹን የመጀመሪያ ክፍል መሙላት አለብዎት, እና የመረጡት አገልግሎት ሰጪ ሁለተኛውን ክፍል መሙላት አለበት። ቅጹ በወላጅ(ዎች) እና በአቅራቢዎች ከተፈረመ በኋላ፣ አቅራቢው የተፈረመውን ቅጂ ለወላጅ ይመልሳል እና ቅጹን ለጉዲፈቻ ድጋፍ አማካሪ ይልካል። የጉዲፈቻ ድጋፍ በቀጥታ ለአቅራቢው ይከፍላል። ቅድመ ፍቃድ የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች በቤት ውስጥ የተረጋገጡ ልምምዶች እና የግለሰብ የማማከር አገልግሎቶን ያካትታሉ።

በማስረጃ ላይ ለተመሰረቱ ልምምዶች፣ ለልጆቻችሁ እንደያእድሜያቸው ስላሉት የሕክምና እርዳታዎች መረጃ ይላክልዎታል። መረጃው የአገልግሎቱን ማግለጫ እና እንዴት አቅራቢ መምረጥ እንደሚችሉ በዉስጡ አካትቷል። የጉድፈቻ ድጋፍ ለሚያገኙ ቤተሰቦች እያገኙት ያሉት አገልግሎቶች የሚከተሉትን አገልግሎቶች ያካትታሉ፡ Promoting First Relationships, Incredible Years, Parent Child Interaction Therapy, Functional Family Therapy, Triple P, SafeCare, እና Family Preservation Services። ብዙ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ አገልግሎቶች በMedicaid ይሸፈናሉ። ምን እንደተሸፈነ ለማወቅ እና አቅራቢውን ለማግኘት የ Apple Health እቅድዎን ያነጋግሩ።

በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የተግባር አገልግሎት ከጨረሱ በኋላ፣ ቤተሰብዎ በግል የምክር አገልግሎት እንዲቀጥሉ ይመከራል። ሁለቱም ሂደቶች የቅድመ-ፍቃድ ጥያቄን ሂደት መከተልን ያካትታሉ።

**Q:** ከማደጎ በኋላ ልጅዎ የነዋሪ ሕክምና ፕሮግራም ካስፈለገውስ?

**A:** በWAC 110-80-0250 ስር፣ የጉዲፈቻ ድጋፍ መርሃ ግብር ለመኖሪያ ሕክምና ምደባዎች መክፈል አይችልም። በሚከተሉት ምክንያቶች ልጅዎ የነዋሪነት ሕክምና አገልግሎቶችን ከጠየቀ፡-

- በልጅዎ የአእምሮ ህመም ምክንያት እባክዎን ወደ ዋናው የኢንሹራንስ ኩባንያዎ ወይም ወደ Apple Health እቅድ ይደውሉ።
- የልጅዎ የአካል፣ የአዕምሮ፣ የእድገት፣ የግንዛቤ ወይም የስሜታዊ የአካል ጉዳት ምርመራ፣ እባክዎን ልጅዎ ለአገልግሎቶቹ ብቁ መሆኑን ለማወቅ ለDevelopmental Disabilities Administration(ልማት አካል ጉዳተኞች አስተዳደር፣ DDA) ይደውሉ።
- ከአእምሮ ሕመም ወይም ከዕድገት እክል ሕክምና ሌላ ፍላጎት፣ እባክዎን በአካባቢያዊው የDCYF Child Welfare ቢሮ የሕፃናት ደህንነት አገልግሎቶችን ይደውሉ።
- በችግር ጊዜ ወይም በከባድ ሁኔታ፣ በባህሪ ጤና እና በማገገም የሚንቀሳቀሰውን Wrap Around Intensive Service(የተጠናከረ የአገልግሎት መጠቃለያ፣ WISe) ፕሮግራምን እራስዎ ማመልከት ይችላሉ **www.hca.wa.gov/health-care-services-supports/behavioral-health-recovery/child-and-youth-behavioral-health**።

ልጅዎ በ CCW-AHCC የተመዘገበ ከሆነ እና ልጅዎ ነዋሪ/ታካሚን ጨምሮ የተጠናከረ የባህሪ ጤና አገልግሎት ያስፈልገዋል ብለው ካመኑ፣እባክዎ ለልጅዎ ትክክለኛ አገልግሎት ለማግኘት እንዲረዳዎ AHCC በ 1-844-354-9876 ወይም **AHCCTeam@coordinatedcarehealth.com** ያግኙ።

## ትምህርት

**Q:** ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ለየትኛውም ልጅ ማንኛውም አይነት የትምህርት ፕሮግራሞች አሉ?

**A:** ከ14 ዓመት በኋላ የማደጎ ወጣቶች ለCollege Bound ስኮላርሺፕ ፕሮግራም ብቁነታቸውን ማስጠበቅ ይችላሉ።

ከኦክቶበር 19 ቀን 2017 ጀምሮ፣ በWashington የጉዲፈቻ ድጋፍ ስምምነት ከ14 ዓመት እስከ 18 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የማደጎ ወጣቶች ለCollege Bound ስኮላርሺፕ ብቁነታቸውን ይቀጥላሉ። ልጅዎ ከዚህ ቀደም ለዚህ የነፃ ትምህርት ዕድል ብቁ መሆኑን ለማወቅ፣ የWashington Student Achievement Council በ1-888-535-0747 ያግኙ እና አማራጭ 1ን ይምረጡ ወይም ኮሌጅ **bound@wsac.wa.gov**ኢሜይል ያድርጉ።

ለCollege Bound ስኮላርሺፕ ብቁ ለመሆን፣ ተማሪዎች ለነጻ ወይም ለቅናሽ ዋጋ ምሳ ብቁ መሆን አለባቸው ወይም በምዕራፍ 13.34 RCW መሠረት ጥገኛ መሆን አለባቸው። ጥገኛ ልጆች፣ ከ7ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ወይም ከ18 እና 21 አመት መካከል ያሉ እና ከሁለተኛ ደረጃ ያልተመረቁ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አቻነት ሰርተፍኬት ያላጠናቀቁ መሆን አለባቸው። ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲመረቁ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመጣጣኝ የምስክር ወረቀት ሲያገኙ ለCollege Bound ስኮላርሺፕ ብቁ ሆነው ለመቆየት፣ ተማሪዎች ከመካከለኛው የቤተሰብ ገቢ 65% ወይም በታች የቤተሰብ ገቢ ሊኖራቸው ይገባል እና በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተሳካ ሁኔታ መመዝገብ አለባቸው። ለተጨማሪ የብቃት መስፈርት እና ስለ College Bound ስኮላርሺፕ ማመልከቻ ሂደት መረጃ፣ እባክዎን **www.wsac.wa.gov/college-bound** ይጎብኙ።

**Q:** ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ለየትኛውም ልጅ ተጨማሪ የትምህርት ፕሮግራሞች አሉ?

**A:** Education and Training Voucher(የትምህርት እና ስልጠና ቫውቸር፣ ETV) ፕሮግራም በማደጎ ውስጥ ለነበሩ እና 16 ዓመት ከሞላቸው በኋላ በማደጎ ለወሰዱ ወጣቶች ይገኛል። ETV ብቁ የሆኑ አሳዳጊ ወጣቶች እውቅና ባለው ኮሌጅ፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ሙያ ወይም ቴክኒክ ኮሌጅ ትምህርታቸው መማር እንዲችሉ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። የETV ፕሮግራም ተማሪዎች ወደ ኮሌጅ ለመግባት የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት በራሳቸው ጥረት ይረዳል። ከፍተኛው የETV ሽልማት በአንድ የትምህርት ዘመን $5,000 ዶላር ነው።

ሽልማቶች ለእያንዳንዱ ተማሪ ልዩ ናቸው እና በምርጫ ኮሌጃቸው በተዘጋጀው የክትትል ፎርሙላ ወጪ እና በፋይናንሺያል ርዳታ ሽልማታቸው ውስጥ ሊኖሯቸው የሚችላቸው ያልተሟላ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

- ETV በአገር አቀፍ ደረጃ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።
- ዕድሜያቸው 21 ዓመት ሳይሞላቸው የተሳተፉ እና የETV ክፍያ የሚቀበሉ ወጣቶች እስከ 23 ዓመታቸው ድረስ ETV'ን ማግኘት ይችላሉ።

## ያማመልከቻ ሂደት

የETV ማመልከቻዎች በጎልማሶች ድህረ ገጽ ላይ ይገኛሉ **www.independence.wa.gov** ወይም የፕሮግራሙን ሰራተኞችን በማነጋገር ግልባጩን ከ **ETVWASH@dshs.wa.gov** መጠየቅ ይችላሉ፦

- የመስመር ላይ ማመልከቻዎች ለመጀመርያ ጊዜ አመልካቾች ብቻ ነው።
- የማሳደሻ ማመልከቻ ተመልሰው ለሚመጡ ለብቁ አመልካቾች ነው የሚሆነው።
- የሩጫ ጅምር/ድርብ ክሬዲት ማመልከቻ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላሉ ተማሪዎች በሩጫ ጅምር ፕሮግራም ውስጥ እንዲካፈሉ ለተፈቀደላቸው እና የኮሌጅ ደረጃ ኮርሶችን ለሚወስዱ ተማሪዎች ነው።
- ቅድሚያ የሚሰጠው የማመልከቻ ዑደት ጃንዋሪ(ጥር) 1 ይጀምራል እና በየአመቱ ኤፕሪል(ሚያዝያ) 30 ያበቃል። ከኤፕሪል 30 በኋላ የገቡት ሁሉም ማመልከቻዎች በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ይቀመጣሉ እና በተገኘው ገንዘብ መሠረት ይሸለማሉ። የማመልከቻው ዑደት በሐምሌ 31 ይዘጋሉ። ከዚህ ቀን በኋላ ምንም አይነት ማመልከቻዎችን አንቀበልም።
- በፌዴራል መመሪያ መሰረት ወጣቶች ለFree Application for Federal Student Aid (ለፌደራል የተማሪ የነጻ ማመልከቻ እርዳታ፣ FAFSA) በየአመቱ መሙላት አለባቸው ኦክቶበር 1 በኋላ ወይም ከዚያ በኋላ 13 ዓመት ከሞላቸው በኋላ ጉዲፈቻ የተቀበሉ ወጣቶች ለፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ ለማመልከት እንደ ገለልተኛ ይቆጠራሉ። ሆኖም ግን፣ ኮሌጆች ተጨማሪ ማረጋገጫ ሊጠይቁ እና የጉዲፈቻው መቼ እንደተፈጸመ ማረጋገጫ ሊጠይቁ ይችላሉ።
- ወጣቶች በየዓመቱ ለፕሮግራሙ እንደገና ማመልከት አለባቸው።



## ይየብቁነት ወጪዎች

ተማሪዎች የETV ሽልማታቸውን አንዴ ከተቀበሉ በሚከተለው እርዳታ ሊጠይቁ ይችላሉ።

- የትምህርት ክፍያ - ሁሉም ሌሎች የገንዘብ ዕርዳታ ዓይነቶች በመጀመሪያ ለትምህርት ክፍያ መተግበር አለባቸው።
- ለመህጻፍት እና አቅርቆቶች
- ለቤት - የኪራይ ተቀማጭ ገንዘብ፣ ወርሃዊ የኪራይ ክፍያዎች እና መገልገያዎች
- ለግሮሰሪ እና ለግል ንፅህና እቃዎች።
- ለመጓጓዣ - የባስ ትኬት፣ በመኪና ኢንሹራንስ፣ ጋዝ፣ ጥገና እና ጥገና ላይ እገዛ
- ለልጅ እንክባካቤ።

## በፖርግራሙ ውስጥ የሚፈለጉ መስፈርቶች እና ቀጣይነት ያላቸው ተሳትፎዎች

ወጣቶች የETV ተሳትፎ ስምምነትን ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። ዋነኞቹ መስፈርቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ወጣቶች የተቋማቸውን Satisfactory Academic Progress(አጥጋቢ የትምህርት እድገት፣ SAP) መስፈርቶች ማሟላት ፣ 2.0 GPA ወይም የተሻለ መያዝ እና ወደ ዲግሪ ወይም ሰርተፍኬት መሻሻላቸውን ማሳየት አለባቸው።
- ወጣቶች ቢያንስ ግማሽ ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ መመዝገብ አለባቸው፣ ይህም ማለት ስድስት ወይም ከዚያ በላይ ክሬዲቶች ማለት ነው።
- ወጣቶች ቢያንስ በአንድ ባለ 100 ደረጃ የኮሌጅ ኮርስ መመዝገብ አለባቸው እንዲሁም የገንዘብ እርዳታ ለማግኘት ብቁ መሆን አለባቸው።
- ወጣቶች በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መጀመሪያ ላይ የክፍላቸውን መርሃ ግብራቸውን እና በእያንዳንዱ የስራ ዘመን መጨረሻ ላይ መደበኛ ያልሆኑ ግልባጮችን ቅጂ ማቅረብ አለባቸው።

ለበለጠ መረጃ፡- **www.independence.wa.gov**ን ይጎብኙ ወይም የፕሮግራሙን ሰራተኞች በ 1-877-433-8388 ወይም በ **kathy.ramsay@dcyf.wa.gov** ይግኟቸው።

## የጉዲፈቻ ማጠናቀቅያ ወጪዎች

**Q:** የጉዲፈቻ ሂደት ማጠናቀቂያ ወጪዎችን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

**A:** የጉዲፈቻ ሂደት ማስጨረሻ ወጪዎች ጉዲፈቻውን ለማጠናቀቅ የአንድ ጊዜ ወጪዎች ናቸው። የጠበቃ ክፍያዎችን፣ የፍርድ ቤት ማቅረቢያ ክፍያዎችን፣ የአካል ወጪን እና የቤት ጥናት ክፍያዎችን በውስጣቸው ያካትታሉ። ለእነዚህ ወጪዎች ማካካሻ ለማግኘት ከፈለጉ ጉዲፈቻው ከመጠናቀቁ በፊት ማመልከቻ ማስገባት አለብዎት። ለአንድ ልጅ የሚከፈለው ከፍተኛው ወጪ $1,500 ዶላር ነው። የጉዲፈቻው ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ማካካሻ ይከሰታል እና በስምምነቱ ውስጥ በተጠቀሰው መጠን ላይ በተጨባጭ ወጪዎች ላይ የተመሰረተ ነው።

**Q:** ክፍያውን ለማረጋገጥ ምን ያስፈልጋል?

**A:** የጉዲፈቻው ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የተፈቀዱ ወጪዎችዎ የሚከተሉትን ስናገኝ ተመልሰው የሚከፈሉ ይሆናሉ፡-

- የተፈረመበት የጉዲፈቻ አዋጁ ቅጂ
- በቅጹ ላይ ላቀረቡት አገልግሎት እንደከፈሉ የሚያሳይ የክፍያ መጠየቂያዎች ቅጂ
- ለተከፈለባቸው አገልግሎቶች ሕጋዊ የሆነ ደረሰኝ፣ ወይም
- የተሰረዘ ቼክ ግልባጭ።

## ስልጠና

**Q:** የልጄን ልዩ ፍላጎቶች በተሻለ ለመረዳት በስልጠናዎች መሳተፍ እችላለው?

**A:** ቤተሰብዎ በAlliance for Child Welfare Excellence(የሕጻናት ደህንነት ልቀት ጥምረት) በ **www.allianceforchildwelfare.org** እና Coordinated Care of Washington(የተቀናጀ የዋሽንግተን እንክብካቤ) - Apple Health Core Connections **www.coordinatedcarehealth.com**። በተሰጡት ሁሉም የተንከባካቢ የሥልጠና እድሎች ላይ የመሳተፍ መብት አላቸው። ለተጨማሪ መረጃ ለጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪዎን ይግኙ።

CCW-AHCC ለወላጆች የሚገኙ በርካታ የመስመር ላይ ስልጠናዎች ያሉት ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥም ስልጠናዎችን ይሰጣል። ለበለጠ መረጃ፣ **CommunityEducation@coordinatedcarehealth.com**ን ያግኙ።

## ተጨማሪ መረጃዎች

**Q:** በፕሮግራሙ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማኝ ችሎት የማግኘት መብት አለኝ?

**A:** ከሚከተሉት ውሳኔዎች ውስጥ አንዳቸውም በፕሮግራሙ የተወሰዱ ከሆነ፣ በAdministrative Law Judge(አስተዳደር ህግ ዳኛ፣ ALJ) ፊት ችሎት እንዲታይ መጠየቅ ይችላሉ፡-

- የልጅዎ የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም የመጀመሪያ ብቁነት ከተከለከለ።
- የፕሮግራሙ አማካሪ ለጽሁፍ ማመልከቻ ወይም የአገልግሎቶች ጥያቄ ምክንያታዊ በሆነ ፍጥነት ምላሽ ካልሰጠ።
- በስምምነቱ ውስጥ ያለውን የክፍያ ወይም የአገልግሎት ደረጃ ለመቀየር ጥያቄ ውድቅ ከተደረገ።
- ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ ደረጃን ለመጨመር ወይም ለመቀነስ ውሳኔ የተደረገው ያለፈቃድዎ ከሆነ።
- የማደጎ ማጠናቀቂያ ወጪዎች ጥያቄ ውድቅ ከተደረገ።
- ልጅዎ ከፕሮግራሙ ከተቋረጠ እና እርስዎ ካልተስማሙ።

**Q:** ችሎት እንዴት መጠየቅ እችላለው?

**A:** የፕሮግራም ውሳኔዎችን በተመለከተ የመስማት መብትህን፣ ችሎት የመጠየቅ ቀነ-ገደብ፣ የመሰማት ጥያቄህ በጽሁፍ መሆን እንዳለበት፣ ጥያቄውን ወዴት እንደምትልክ እና ጥያቄውን በቃል ማቅረብ እንደምትችል በጽሁፍ ማሳወቂያ ይደርስሃል። እንዲሁም ወደ Office of Administrative Hearings (የአስተዳደራዊ ችሎት ቢሮ፣ OAH) መጻፍም ይችላሉ በዚህ በኩል፡-

Office of Administrative Hearings
PO Box 42489
Olympia, WA 98504-2489

ሁሉም የOAH ቢሮዎች የነጻ መስመር ቁጥሮች አሏቸው። በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ቢሮ መደወል ጥሩ ነው። ለአከባቢዎ ቅርብ የሆነውን የAdministrative Hearings ቢሮ ለማግኘት ፣እባክዎን ድህረ ገጹን **www.oah.wa.gov** ይመልከቱ።

**Q:** የሰሚ ችሎት ለማግኘት ከጠየኩኝ በኋላ ምንድን ነው የሚፈጠረው?

**A:** Office of Administrative Hearings(የአስተዳደር ችሎቶች ጽሕፈት ቤት፣ OAH) ችሎት ቀጠሮ ይይዛል እንዲሁም ችሎቱ ከተሰማበት ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ ጋር የችሎት ማስታወቂያ ይልካል። በማስታወቂያው ውስጥ የተካተተው ስለ ችሎቱ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ነው። በወስጡ ለተካተተው ብሮሸር ልዩ ትኩረት ይስጡ። ሁሉንም ያንብቡ። በጥንቃቄ ይንብቡ።

ቀጥሎም፣ ከDCYF የመጣው የችሎት ተወካይ ችሎቱን የጠየቀውን ሰው እና ማንኛውም ፍላጎት ያለው አካል በጉዳዩ ላይ ለመወያየት እና አለመግባባቱን ለመፍታት ይሞክራል። የDCYF ተወካይ ስልክ ቁጥር በችሎት ማስታወቂያ ላይ ተጽፏል። እንዲሁም ግንኙነትን ማስጀመር ይችላሉ።

ፋይልዎን ለመገምገም እና ለችሎቱ ጠቃሚ ናቸው ብለው ያመኑባቸውን ሰነዶች ቅጂ ለማድረግ ከፈለጉ፣ ይህን ለማድረግ ጊዜ ለማዘጋጀት ለDCYF ተወካይ መደወል አለብዎት።

አንዳንድ ጊዜ Administrative Law Judge(የአስተዳደር ህግ ዳኛ፣ ALJ) የቅድመ ችሎት ኮንፈረንስ ቀጠሮ ይይዛል። እነዚህም ሁልጊዜ በስልክ የሚከናወኑ ናቸው። ALJ የቅድመ ችሎት ጉባኤ ካቀደ፣ ስለሚጠበቀው ነገር መመሪያዎች በጊዜ መርሐግብር ማስታወቂያ ውስጥ የሚካተቱ ይሆናሉ።

**Q:** ሌላ ሰው እኔን እንዲወክለኝ ከፈልኩስ?

**A:** በራስዎ ወጪ ጠበቃ እርስዎን እንዲወክል መቅጠር ይችላሉ። ነጻ እና አነስተኛ ክፍያ ያላቸው የሕግ ድጋፍዎች በ **http://oah.wa.gov** ድር ገጽ ላይ፣ "How do I Find legal Assistance?" የሚለው ዋና ገጽ ስር ይገኛሉ። ሌላ ሰው እንዲወክልዎ ከፈለጉ፣ ተወካይዎ በችሎቱ ላይ መገኘት አለበት።



**Q:** የጉዲፈቻው ሂደት እንደተጠናቀቀ፣ የማህበራዊ ዋስትና አስተዳደርን ማነጋገር አለብኝ?

**A:** አዎ፣ ልጅዎ በጉዲፈቻ ሲወሰድ፣ የጉዲፈቻው ሂደት መጠናቀቁን ለማሳወቅ የማህበራዊ ዋስትና አስተዳደርን ማነጋገር አለቦት። አስተዳደሩ የልጁን መዝገብ በአዲሱ መለያ መረጃ ያዘምናል እና የዘመነ ካርድ ያወጣል።

አንዴ መረጃውን ከማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ለልጅዎ ካዘመኑ በኋላ፣ እባክዎን Medicaid እና የማደጎ ድጋፍ አማካሪዎን ያሳውቁ።

**Q:** የጉዲፈቻ ታክስ ክሬዲት ምንድን ነው?

**A:** ምናልባት የጉዲፈቻ ታክስ ክሬዲት ለመውሰድ ይችሉ ይሆናል። የጉዲፈቻ የግብር ጥቅማ ጥቅሞች ሁለቱንም ብቁ የሆነ ልጅ ለማደጎ ለሚያወጡት የጉዲፈቻ ወጪዎች የታክስ ክሬዲት እና በአሰሪ ለሚሰጠው የማደጎ ዕርዳታ ከገቢ መገለልን ያጠቃልላል።

የበለጠ ጥልቅ እና ግላዊ መረጃ ለማግኘት Internal Revenue Service(የውስጥ ገቢ አገልግሎት፣ IRS) ወይም የግብር አማካሪዎን ያማክሩ

**Q:** ወደ ሌላ ቦታ ከሄድኩኝ Adoption Support(የማደጎ ድጋፍን) ማሳወቅ አለብኝ?

**A:** እንደ የህክምና እና ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያ ያሉ የፕሮግራም አገልግሎቶችን ለማቆየት አዎ፣ የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪዎን በጽሁፍ ማሳወቅ አለቦት። የUS(አሜሪካን) ፖስታ አገልግሎት ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያዎችዎን አያስተላልፍም። ቀጥተኛ ተቀማጭ ገንዘብ ካለዎት እና አማካሪዎን ሳያሳውቁ ከተንቀሳቀሱ የተሻሻለው አድራሻዎ እስኪደርስ ድረስ ወርሃዊ የገንዘብ ክፍያዎ ሊቆይ ይችላል።

## ከክልሉ ወጣ ሲሉ

**Q:** በአዲሱ ስቴት የMedicaid ሽፋን የሚጀምረው መቼ ነው?

**A:** በጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ ሁሉም ልጆች በMedicaid በኩል ለህክምና እርዳታ ብቁ ይሆናሉ። ቤተሰቡ ከWashington ስቴት ውጭ የሚኖር ከሆነ እና የFederal IV-E የማደጎ እርዳታ ጥቅማ ጥቅሞችን እየተቀበለ ከሆነ፣ Medicaid የሚከፈለው በState of residence(መኖሪያ ግዛት) ነው። የFederal IV-E ውሳኔ በእርስዎ የጉዲፈቻ ድጋፍ ስምምነት ላይ ተመዝግቧል። ስለዚህ ሁኔታ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ስለ እንቅስቃሴው በሚያነጋግሯቸው ጊዜው፣ እባክዎን አማካሪዎን ይጠይቁ።

ልጁ ለፌዴራል IV-E የማደጎ ድጋፍ ጥቅማጥቅሞች ብቁ ካልሆነ፣ ያ ግዛት የተገላቢጦሽ የMedicaid ሽፋን ካለው የMedicaid ጥቅማ ጥቅሞች በቀጥታ ከWashington ስቴት ወይም ከመኖሪያ ግዛት ይሰጣል። በWashington's Medicaid Plan ውስጥ የተካተቱ የMedicaid ጥቅማ ጥቅሞች፣ ነገር ግን በነዋሪው ስቴት Medicaid እቅድ ያልተካተተ ወይም የተገደበ በWashington ስቴት Medicaid ፕሮግራም በኩል ይገኛል። በተጠየቀ ጊዜ፣ የWashington ስቴት ጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም ሰራተኞች የMedicaid ሽፋን ለማግኘት እንዲረዳቸው ከነዋሪው ግዛት ጋር ግንኙነትን ያመቻቻሉ። የMedicaid ሽፋን ከWashington ስቴት ሽፋኑ በነዋሪው ግዛት እስኪራዘም ድረስ ይቀጥላል።

*ጠቃሚ ምክር፦ ልጅዎ ወርሃዊ መድሃኒት የሚፈልግ ከሆነ እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ በቂ ማግኘቱን ያረጋግጡ።*

## የማህበረሰብ አገልግሎቶች/ድጋፍዎች

**Q:** የድጋፍ ቡድኖችን እንዴት ማግኘት እችላለው?

**A:** የማደጎ፣ ምግዚትነት፣ አሳዳጊ እና ዘመድ ተንከባካቢዎችን የሚያገለግሉ የድጋፍ ቡድኖች በስቴቱ ዙሪያ እየተዘጋጁ ናቸው። ስለነዚህ ቡድኖች መረጃ ለማግኘት፣ በአካባቢዎ የሚገኘውን የDCYF ቢሮ ወይም የአሳዳጊ ወላጅ እና ተንከባካቢ ድጋፍ መስመርን በ1-800-301-1868 ያግኙ።

**የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወስ አለብን፦**

በግዛቱ ውስጥም ሆነ ወደ ሌላ ግዛት ሲሄዱ አድራሻዎችን ሲቀይሩ ማስታወስ ያለብዎት የጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪዎን ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። ልጅዎ 18 ዓመት ሲሞላው እና አሁንም ትምህርት ቤት ከሆነ፣ ለኤክስቴንሽን ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ ለጉዲፈቻ ድጋፍ ፕሮግራም አማካሪዎ ይደውሉ።



# የመስመር ላይ ሪሶርሶች

## የCenter for Adoption Medicine(የጉዲፈቻ መድሃኒት ማዕከል)ዌብሳይት

በWashington ዩኒቨርሲቲ፣ በጉዲፈቻ እና በሕፃናት ሕክምና ውስጥ ለሕክምና እና ልማት ጉዳዮች ያለን ሪሶርስ።

**www.adoptmed.org/home**

## ያአዕምሮ ጤና አገልግሎቶች

Health Care Authority(የጤና እንክብካቤ ባለስልጣን፣ HCA) በApple Health (Medicaid) ለተመዘገቡ ሰዎች ለአእምሮ ጤና አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል።

**www.hca.wa.gov/health-care-services-supports/behavioral-health-recovery/mental-health-services**

## North American Council on Adoptable Children(የማደጎ ልጆች ላይ የሰሜን አሜሪካ ምክር ቤት)

በአሜሪካ የማደጎ እንክብካቤ ሥርዓት ውስጥ ላሉ ልጆች የማደጎ መረጃ እና አገልግሎቶችን ይሰጣል።

**www.nacac.org**

## National Organization on Fetal Alcohol Syndrome(የፅንስ አልኮል ሲንድሮም ብሔራዊ ድርጂት) – የWashington እስቴት

NOFAS Washington የፅንስ አልኮሆል ስፔክትረም ዲስኦርደር ላለባቸው ግለሰቦች፣ ተንከባካቢዎቻቸው እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪዎች የድጋፍ እና የግብዓት ምንጭ ነው።

**www.nofaswa.org**

## Child Welfare Information Gateway (የልጅ ደህንነት መረጃ መግቢያ)

ከማደጎ ወስደው ማሳደግን ጨምሮ፣ በሁሉም የሀገር ውስጥ እና የሀገር ከሃገር ዉጪ ጉዲፈቻ ላይ ያሉ ግበዓቶች(ሪሶርሶች)። ለወደፊት እና ለአሳዳጊ ወላጆች የሚሆኑ መረጃዎች፣ የማደጎ ቤተሰቦችን በመመልመል ላይ የተወለዱ ዘመዶችን እና ለባለሙያዎች ሀብቶችን ስለመፈለግ ያለ መረጃ፣ ልጆችን እና ወጣቶችን ስለ ማዘጋጀት፣ የወለዱ ወላጆችን ስለመደገፍ፣ ከጉዲፈቻ በኋላ አገልግሎቶችን መስጠትን በውስጡ ያካትታል።

**www.childwelfare.gov/adoption/index.cfm**

## የWashingont ስቴት Medicaid፡-

በWashington ስቴት ውስጥ የ ProviderOne Medicaid አገልግሎት ሰጪዎችን ለማግኘት የሚያስችል ሪሶርስ።

**https://fortress.wa.gov/hca/p1findaprovider/**

## አሳዳጊ ወላጅነት & የዝምድና እንክብካቤ

በማህበራዊ አገልግሎት ሀብቶች ላይ መረጃን ይሰጣል።

**www.dcyf.wa.gov/services/foster-parenting**



**www.dcyf.wa.gov**

*የዚህን ሰነድ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ማግኘት ከፈለጉ ፣ እባክዎን **DCYF Constituent Relations**(አባል ግንኙነቶች)ን በ(1-800-723-4831 | 360-902-8060 ፣ **ConstRelations@dcyf.wa.gov**) ያነጋግሩ።*

DCYF PUBLICATION CWP_0063 | DSHS 22-1211 AM (06-2021) Amharic